


## 40-1

# ከግል ጥቅም የራቀ አገልግሎት እንዲኖረን

ከሚጠቀሱ…

- “ቃሉን ስበክ ቢመችም ባይመችም በማንኛውም ጊዜ ተግተህ ሥራ፤ እያስረዳህ፣ እየገሰጽህና እየመከርህ በትዕግሥትና በማስተምር ጽና” (2 ጢሞ 4፥2)
- “ዓሣ በማጥመድና እንደ ጅል ከባሕር ዳር በመቆም መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት አለ” ስቲቨን ራይት
- “በደስታ ልቡ የተሞላ ሰው ባይሰብክም እየሰበከ ነው” ሚዘር ትሬሳ
- “የምሰብከው ከሌለኝ እንደ አንበሳ እጮሃለሁ” ሉተር
- “መስበክ መወደድና የምንሰብክላቸውን ሰዎች መውደድ ሁለቱ የተለያዩ ነገሮች ናቸው” ሲሲል
- “እውነተኛ ሠራተኛ “ወንዙ ቆሽሿል” የሚለው ሳይሆን ወንዙን የሚያጸዳው ነው” ሮስ ፐሮ
- “እውነት ያሳምማል” አርኖልድ ግላሶ

- “ጌታ ለአገልግሎት ጠርቶኛል”
- “አገልግሎት አለብኝ”
- “አገልግሎቴን የሚነካብኝን ሰው አልወድም”
- “ከአገልግሎቴ የሚበልጥብኝ ነገር የለም”

በአሁኑ ጊዜ ይህን ዓይነቱ አነጋገር በብዙ ክርስትያኖች ዘንድ የተለመደ ሆኗል። የጊዜው ልማዳዊ የሃይማኖት ቋንቋ ሆኖ ይሆን ወይንስ እውነተኛ “አገልግሎት” ምን እንደሆነና ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍል ገብቷቸው ነው? በዚህ ጥናታችን እውነተኛ አገልግሎት ምን እንደሆነና እንዳልሆነ ከእውነተኛ አገልጋይ ምን እንደሚጠበቅና እንዲሁም አገልጋይን ሊያደክሙ ወይንም ሊያጠፉ የሚችሉትን ነገሮች እንመረምራለን።

## ለሰፊው መከር በቂ አገልጋይ የለም

በኢትዮጵያ ውስጥ ለሆነው ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ምክንያት የሆኑ ለዓይን ጎልተው የሚታዩ ሰዎች አይደሉም። እንደ ቢሊግራሃም ዓይነት ታዋቂ ሰባኪያን ተነስተው ትላልቅ ስብሰባዎችን (ራሊዎችን) አላካሄዱም። ይህን ስል ታላላቅ ሰባኪዎች አያስፈልጉንም ማለቴ አይደለም። በኢትዮጵያ ውስጥ ለተፈጸው ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ምክንያት የሆኑት የተወሰኑ አገልጋዮች ሳይሆኑ፥ አማኞች በሙሉ መሆናቸውን ለመግለጽ ብቻ ነው። “ኢየሱስ ያድናል” ብሎ መመስከር ቀርቶ የራስንም የክርስትና ሕይወት ጠብቆ መኖር አስቸጋሪ በሆነበት ዘመን፥ ያለፍርሃት እያንዳንዱ አማኝ ተገልጋይ ብቻ ሳይሆን ሁሉም አገልጋይ መሆኑን ተገንዝቦ ለነፍሳት በመመስከሩ ብዙ ነፍሳት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊጨመሩ ችለዋል። ሳይንቲፊካዊ የሆነ ምርምር ባናደርግም፥ ጌታን ካወቁት መካከል በግል ሰዎች ተመስክሮላቸው የዳኑ ከመቶ ሰማንያ (80%) ወይንም ከዚያ እንደሚበልጡ እንገምታለን። አማኞች ሁሉ ለወንጌል ስርጭት ተሳታፊዎች በመሆናቸው አገልጋይ አይስፈልግም ማለት አይደለም። ከምንጊዜውም ይበልጥ በኢትዮጵያውያን መካከል ቁጥር ስፍር የሌላቸው አገልጋዮች የሚያስፈልጉበት ዘመን አሁን ነው። በወቅቱ ያሉት መሪዎች ትኩረት ሊሰጡበት የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር፥ ትላልቅ ስብሰባዎችን (ራሌዎችን) ማካሄድ ሳይሆን፥ በየቀኑ የሚጨመሩትን ነፍሳት ኮትኩተው የሚያሳድጉትን አገልጋዮች ማሰልጠንና ወደ አገልግሎት የሚመጡበትን መንገድ መፈለግ ነው። የአገልጋይ እጥረት ባለበት አካባቢ ብዙ የተለያዩ ችግሮች እንደሚፈጠሩ ግልጽ ነው። ችግሩ ምዕመናኑ የሚያገለግሏቸው በቂ የሆኑ አገልጋዮች ማጣታቸው ብቻ ሳይሆን፥ ያሉት አገልጋዮች እንደ ጥሪአቸውና እንደ ስጦታቸው በአግባቡ ማገልገል አለመቻላቸው ነው።

### 1) አገልግሎት ሙያ አይደለም

በዓለም ውስጥ ሁሉ አቅሙና ችሎታቸው በሚፈቅደው መሠረት ደስ በሚለው ሙያ () ሠርቶ መኖር መሠረታዊ

መብቱ ነው። በሚወደው የሙያ ዘርፍ ተሰልፎ ለመሥራት የሚያበቃውን እውቀት ለመቅሰም ረጅም ዘመን በትምህርት ላይ ያሳልፋል። ሀኪም፣ መሃንዲስ፣ አስታማሚ፣ መምህር ወዘተ ሆኖ ሁሉም እንደየምርጫው ሠርቶ መኖር ይላል። አገልግ ሎትስ ልክ እንደ አንድ ሙያ የመረጠ ሁሉ የሚገባበት የሥራ መስክ ይሆን? አንድ ሰው ለአገልግሎት የሚያዘጋጀውን ትምህርት ቢቀስም አገልጋይ መሆን ይችላል? አይመስለኝም። አገልግሎት ከሌላው የሥራ ዘርፍ የሚለዩበት አንደኛውና ትልቁ ተሳታፊዎቹ ወደ አገልግሎት የሚገቡት መርጠው ሳይሆን፥ ጥሪ ተደርጎላቸው ብቻ ነው። የእሥራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ባርነት ነጻ እንዲያወጣ እግዚአብሔር ሙሴን መሪ ሲያደርገው በጥሪ ነው። “እነሆ ሕዝቤን ከግብጽ ምድር ታወጥ ዘንድ ወደ ግብጽ ንጉሥ እልክሃለሁ” (ዘጸአት 3፥10) አለው። ኢያሱም ሙሴ የጀመረውን ሥራ መቀጠል የቻለው ከእግዚአብሔር ጥሩ ተደርጎለት ነው (ኢያሱ 1)። ምድያማውያን የእሥራኤልን ሕዝብ ባስጨነቁአቸው ጊዜ ጌዲያንን “… ሂድ ባለህ ብርቱ ኃይል ሁሉ በመጠቀም እሥራኤላውያንን ከምድያማውያን እጅ ታደግ፤ እነሆ እኔ ራሴ ልኬሃለሁ…” (መሳፍንት 6፥14) ሲለው እግዚአብሔር እንደ ጠራው እያናለን።

መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናነብ በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዘርፍ የተሰለፉ አገልጋዮች እንዲሁም በአዲስ ኪዳን የነበሩ ሐዋርያት ሁሉ ወደ አገልግሎት የገቡት እነርሱ መርጠው ሳይሆን ከጌታ ጥሪ ተደርጎላቸው ነው። በእናም ዘመን ያሉ አገልጋዮች ወደ አገልግሎት የሚመጡት ከእግዚአብሔር ጥሪ ተደርጎላቸው ነው። ይህን ስንል በአገልግሎት የተሰለፉ ሁሉ ከጌታ ጥሪ ያላቸው ናቸው ማለታችን አይደለም። ያለጥሪአቸው የተሰማሩ ብዙ አገልጋዮች አሉ። አንዳንድ ችግሮችም በአገልግሎት ዙሪያ እንዲከሰቱ ከሚያደርጉት ልዩ ልዩ ምክንያቶች አንደኛው ጥሪ ሳይኖራቸው ወደ አገልግሎት በሚመጡ አገልጋዮች ምክንያት ነው። እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ ሰጠራ “እሺ” ለማለት የራስን ፈቃድ ትቶ በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ መመራትን ይጠይቃል። በሌላ የሥራ መስክ ብቃትና ችሎታ እያለው በምድር ጥቅም ያለበትን ሥራ መሥራት ትቶ፣ ተራ ሰባኪ ሆኖ መኖር፣ አዕምሮ ያለው ሰው የሚመርጠው ምርጫ ስላልሆነ፥ በዓለም ዘንድ ሞኝ ያሰኛል። ለዚህ ነው እውነተኛ አገልጋይ መሆን ዋጋ የሚያስከፍለው።

## 2) ደካማዎች ብቻ የሚሠሩት አይደለም

እግዚአብሔር ለከፍተኛ አገልግሎት የመረጣቸው አብዛኞዎቹ ከዝቅተኛ ነገድና ቤተሰብ የወጡ፥ ፈሪዎች፣ ተብታባዎችና የተለያየ የራሳቸው የሆነ ጉድለት የነበራቸው ነበሩ። እግዚአብሔር ይህን ያደረገው <u>ሰው እጥቶ</u> (ይህ አባባል ቢለወጥ) ሳይሆን ሆን ብሎ ደካማዎችን መርጦ ነው። ብርቱዎች ብርቱ ስለሆኑ የተመረጡት ይመስላቸዋል፤ ደካማዎች ግን የሚኮሩበት ነገር ስለሌላቸው በዚህ ምክንያት ተመረጥኩ ብለው በራሳቸው አይኩራሩም። ኢየሱስ በአዲስ ኪዳን ደቀ መዛሙርቱ እንዲሆኑ የመረጣቸው ዓሣ አጥማጆች፣ ቀራጮችና በሕብረተሰቡ ጎልተው የማይታዩትን ነበር። ይሁን እንጂ አንድ ነገር ልብ ያላልነው እነዚያ ደካማዎች የነበሩ በጌታ እጅ ውስጥ ሲገቡ ብርቱዎች ብልሆችና አዋቂዎች የሆኑ መሆናቸውን ነው። በዚህም ምክንያት ነው በሚናገሩትና በሚጽፉት ብዙዎችን ማሳመን የቻሉት።

እግዚአብሔር ብርቱዎችን ለማሳፈር ደካማዎችን ይመርጥ እንጂ፥ ወደ አገልግሎት እንዲገቡ የሚመለመሉት ሁሉ ደካማዎች ትምህርትና እውቀት የሌላቸው ብቻ ናቸው ማለት አይደለም። ይህ እውነት ቢሆን ኖሮ በታላቁ ገማሊል ሥር የተማረው ጳውሎስና እንዲሁም ሀኪም የነበረው ዶክተር ሉቃስ በክርስቶስ አገልግሎት ውስጥ ስፍራ አይኖራቸውም ነበር። በዘመናችን በዓለም ውስጥ ያለውን እውቀት የቀሰሙ፣ ጥበበኞችና አዋቂዎች ለክርስቶስ ሲሉ ሁሉን እንደ “ፋንድያ” ቆጥረው በምድር ክብርና ዋጋ የሌለውን አገልግሎት የመረጡ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ናቸው። በዘማናችንም ወደ አገልግሎት የሚገቡትን ሁሉ ደካሞች፣ ያልተማሩ፣ የአዕምሮ ብስለት የሌላቸው በሌላ የሥራ መስክ ቢወዳደሩ ብቃት የሌላቸው በመሆናቸው ብቻ ወደ አገልግሎት እንደተሰማሩ አድርጎ መገመት ትልቅ ስህተት ነው።

## 3) አገልግሎት መክበሪያ አይደለም

አገልጋይ መሆን ማለት አሽከር፣ ባርያ መሆን ማለት ነው። ባርያ ወይንም አሽከር መሆን ደግሞ ክብር የሌለበት ስለሆነ ማንም አይመርጠውም። የአገልግሎትን ትክክለኛ ትርጉም ያላወቁ አንዳንድ ሰዎች ግን አገልግሎትን የስማቸው መጠሪያ በሕዝብ ዘንድ ጎልቶ መታያ፣ ክብር የሚያገኙበት መሣሪያ አድርገው ሲጠቀሙበት ይታያል። የክብር ፍላጎት ጥማት ያለበት ሰው የጨው ውሃ እንደጠጣ ሰው ነው። የጨው ውሃ የሚጠጣ ሰው በጠጣው ቁጥር የውሃ ጥሙ እየጨመረ ይመጣል እንጂ አይረካም። በዘመናችን በአገልግሎታቸው ብዙዎቹን ይደርሱ የነበሩት እሩጫቸውን ሳይጨርሱ ተሰነካክለው የወደቁት ከምክንያቶቹ አንደኛው የክብር (የኃይል) ጥማታቸው አይሎ ከመስመር ስላስወጣቸው ነው። እግዚአብሔር ሳያከብረው ክብርን ከሰው ለማግኘት የሚጥር አገልጋይ ክብርን የማያገኝ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በሚያዳልጥ መንገድ ላይ የቆመ ሰው ነው።

### 4) ሌላ ሥራ ሲጠፋ የሚገባበት አይደለም

በየሥፍራው የአገልጋይ እጥረት አለ። ይሁን እንጂ የአገልጋይ እጥረት ስላለ ብቻ ሥራ ፈት ሁሉ የሚገባበት አይደለም። በአሁኑ ጊዜ ብዙዎች አገልጋይ ለመሆን ይፈልጋሉ። ለምን ወደ አገልግሎት ለመግባት እንደፈለጉ ግን እራሳቸውን ይመርምሩ። በዓለም ዙሪያ የኢኮኖሚ ሁኔታ በአሁን ጊዜ መጥፎ ነው። ብዙ ወጣቶች በአገራችን ሥራ የላቸውም። ሥራ የነበራቸውም አንዳንዶቹ ጡረታ ተብለው ወጥተዋል። ሥራ ያላቸውም ቢሆኑ አንድ ቀን ከሥራ እወጣ ይሆናል የሚል ስጋት አለባቸው። ከሥራ እወጣለሁ የሚል ሥጋት የሌለበት በአገልግሎት የተሰማራ ሰው ብቻ ነው ብለው ያስባሉ። ነግዶና አትርፎ መኖር ደግሞ ከችሎታቸውና ከአቅማቸው በላይ ነው። ታዲያ እንደነዚህ ዓይነቶች ወደ አገልግሎት ውስጥ ቢገቡ ምን ክፋት አለበት? ክፋት የለበትም፤ ግን ወደ አገልግሎት ለመግባት የፈለጉበት ምክንያት (motive) ትክክል አይደለም። እንዲሁም በውጪ አገር የሚኖሩ፣ ሠርቶ፣ ኑሮን አሸንፎ መኖር፣ በተለይ ተፈላገውን ዓይነትና አጥጋቢ የትምህርት ዝግጅት ለሌላቸው ቀላል አይደለም። አንዳንዶቹ የዕለት ቀዳዳቸውን ለመድፈን ሁለት ወይንም ሦስት ሥራ በግድ መሥራት አለባቸው። የሚያገኙትም የሥራ ዓይነት በጣም ከባድ ጉልበት የሚጠይቅ ነው። በዚህ ዓይነት የውጥረት ኑሮ ውስጥ ለሚኖሩ የሚዝናኑበት ቀርቶ ሰውነታቸውን የሚያሳርፉበትን ጊዜ እንኳን የላቸውም። በትምህርት ራሳቸውን አሻሽለው የተሻለ ሥራ እንኳን እንዳይዙ የመማሪያ ጊዜና ገንዘቡ የላቸውም። በዚህ ዓይነት የወደፊቱም ጨልሞ ስለሚታያቸው ተስፋ በመቁረጥ ሕይወት ውስጥ የሚኖሩ ብዙዎች ናቸው። ይህን ዓይነት ውጥረት ባለበት ኑሮ ውስጥ ከመኖር "መልካም ሥራ እስከ ሠሩ ድረስ ምን አለበት? ጌታን ቢያገለግሉ?" የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። በዚህ ዓይነት ምክንያት ብቻ ወደ አገልግሎት የሚገቡ ሰዎች አገልጋይ የሆኑት ጌታ ጠርቷቸው ሳይሆን እራሳቸውን የጋበዙ ናቸው። እውነተኛ ጥሪ ሳይኖረው በችግር ምክንያት ብቻ ተገፍቶ ወደ አገልግሎት የሚገባ አገልጋይ፥

ሀ) ከነፍሳት ይልቅ ትኩረት የሚያደርገው ገንዘብ ላይ ይሆናል። ትክክለኛ ጥሪ የሌለው አገልጋይ ለመንጋው በመንከባከብ ፈንታ ትኩረት የሚሰጠው የኑሮውን ቀዳዳ የሚደፍንበትን መንገድ መፈለጉ ላይ ነው። ይህንንም እግዚአብሔር ይጠላል። "*መንጋውን መንከባከብና መጠበቅ ትታችሁ ራሳችሁን የምትጠብቁ እናንተ የእሥራኤል እረኞች ወዮላችሁ! ወተቱን ትጠጣላችሁ፣ ከጠጉራቸው የተሠራውንም ሱፍ ትለብሳላችሁ፤ የሰባውንም በግ አርዳችሁ ትበላላችሁ፤ ነገር ግን በጎችን በማሠማራት አትጠብቁም፤ ለደከሙት እንክብካቤ አላደርጋችሁላቸውም፤ የታመሙትን አላዳናችሁም፤ ይህን በማድረግ ፈንታ በግፍና በጭካኔ ገዛችኋቸው፤ የምድር አራዊትም በጫጭቀው በሉአቸው*" (ሕዝ 34፥2-5)።

ለ) አገልግሎት የዕለት እንጀራውን የሚያገኝበት ስለሆነ፥ ያን ይነካብኛል ብሎ ከሚያስበው ኃይል ጋር በቀላሉ ይጋጫል። ስልጣኑና ኃይሉ እንዳይነካበት የተለያየ ዘዴና ብልሃት ይጠቀማል። በሚያገለግላቸው ሰዎች ላይ ከባድ የአገዛዝ ቀንበር ይጭናል። አገልጋይ የተጠራው የእግዚአብሔር መንጋ እንዲጠብቅ፣ እንዲያገለግል፣ እንጂ በኃይል እንዲገዛ፣ ኃይሉን እንዲያሳይ አይደለም። መንጋው እንዲወደው እንጂ እንዲፈራውና እንዲንቀጠቀጥለት አይደለም። "*በአደራ የተሰጣችሁን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፣ መንጋውን የምትጠብቁትም በግድ ሳይሆን እግዚአብሔር በሚፈልገው ዓይነት በፈቃደኝነት ይሁን ለገንዘብ በመስገብገብ ሳይሆን ለማገልገል ባላችሁ ፍላጎት ይሁን። እንዲሁም በእናንተ ኃላፊነት ሥር ያሉትን ጨቁኖ በመግዛት ሳይሆን ለመንጋው መልካም ምሳሌነትን በማሳየት ይሁን*" (1ጴጥ 5፥2-3)።

ሐ) እውነተኛ ጥሪ ሳይኖረው አገልግሎት ውስጥ የሚሰማራ፥ ትኩረት የሚሰጠው የሚያገኘው ጥቅም ላይ ስለሆነ፥ እቤታቸው ሄዶ የሚጠይቃቸው፣ የሚያስተምራቸውና የሚያጽናናቸው ሀብታሞች ወይንም ጥሩ ኑሮ አላቸው ብሎ የሚገምታቸውን ሰዎች ብቻ ይሆናል። ገንዘብ የሌላቸውንና ደካማ ኑሮ ያላቸውን ሰዎች ግን ሄዶ በመጎብኘት ጊዜ ማጥፋት አይፈልግም። ስለ እንዲህ አይነቱ አገልጋይ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል "*መንጋውን ለከዳ፣ ለእንደዚህ ዓይነቱ ዋጋቢስ እረኛ ወዮለት! እጁን በሰይፍ ይቆርጣል፤ ቀኝ ዓይኑም ይወጣል፣ ክንዱ በፍጹም ይዝላል፤ ቀኝ ዓይኑም ጨርሶ ይጠፋል*" (ዘካርያስ 11፥17)።

..............................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**